

# የግንዛቤ ማስጨበጫ

## ለአይ ፒ ኤም ኤስ ፕሮጀክት የተመረጡ ወረዳዎች ውስጥ የስርዓት ፆታ ግንዛቤን የማስረፅ ተግባራት

### በአይ ፒ ኤም ኤስ ፕሮጀክት ውስጥ የስርዓት ፆታ ግንዛቤን የማስረፅ ተግባር ያስፈለገበት ምክንያት

- የስርዓተ ፆታ ግንዛቤ መዳበር በስራ ጫና በሃብት አጠቃቀምና አከፋፈል በኩል መኖር ስለሚገባው የግንኙነት አይነት በማስገንዘብ ረገድ ለግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ፡ መጐልበት ከፍተኛ ሚና ስለሚኖረው

- ሴቶች በአብዛኛው የሳይንስና ቴክኖሎጂ በረከቶች እንዲሁም የተሻሻሉ አገልግ ሎቶች ተጠቃሚ የሚሆኑባቸው አጋጣ ሚዎች በጣም ውስን በመሆናቸውና የረድኤቶቹ ተቋዳሽ ባለመሆናቸው

- ይህ ሁኔታ በችልታ ከታለፈ ቀጣይነት ያለው ገበያ መር ግብርና የማየት ሕልማችንን ሊያመክነው ይችላል

- እንደ /PASDEP/ ከሆነ፤ በ2010 ዓ.ም. 30% የሚሆኑት በአባወራዎች የሚተዳደሩ ሴት አራሾች እና መቶ እጅ በእማወራዎች የሚተዳደሩ ሴት አራሾች ገጠሩን በአማከለ የልማት እቅድ ውስጥ ተሳታፊ ይሆናሉ

### በአይ ፒ ኤም ኤስ ፕሮጀክት የተመረጡ ወረዳዎች ውስጥ የስርዓተ ፆታ ግንዛቤን የማስረጽ አላማዎች

- ከፆታ እይታ አኳያ ቅድሚያ ሊያገኙና በአይ ፒ ኤም ኤስ ሊደገፉ የሚገባቸውን የአቅርቦት አይነቶችና አገልግሎቶች ለይቶ ማወቅ

- በተመረጡ ወረዳዎች ውስጥ ያሉ ባለድርሻዎች በግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ ውስጥ የሚነሱ የፆታ ጥያቄዎችን መለየት የሚያስችላቸውን ክህሎት እንዲያዳብሩ መርዳት

- ወንዶችና ሴቶች በማናቸውም የፕሮጀክት እንቅስቃሴዎች ውስጥ እኩል ሊሳተፉ የሚችሉበትን እድል መፍጠር

- በግብርና ሥራ ውስጥ ያሉ ሁሉ ስለ ፆታ ምንነት ያላቸውን ግንዛቤ እንዲያዳብሩ አስተዋፅኦ ማበርከት

### የግንዛቤ ማስጨበጫ ሰነድ አጠቃቀም

- ይህ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሰነድ የስርዓተ ፆታን ግንዛቤ በማስረጽ ረገድ የበርካታ እንቅስቃሴዎችን ዝርዝር ያካተተ ሲሆን፤ የአይ ፒ ኤም ኤስ የተግባር እቅድ በሚነደፍበት ወቀተ ማለትም ስልጠና፣ የመስክ ጉብኝትና የአዳዲስ ቴክኖሎጂ ውጤቶች ትውውቅ መርሐ ግብሮች ሲነደፉ መጤን ይኖርበታል

- የስርዓት ፆታ ግንዛቤን ለማስረጽ የሚረዱ የተግባር ንድፎች ሲሰሩ የመከታተያ ቅጹን አጠናቆ መሙላት ተገቢ ነው

1. ዓላማ:- ቅድሚያ በሚሰጣቸው ተግባራት የስራ እቅዶች ውስጥ የፆታን ጥያቄ ከግምት ውስጥ ማስገባት

ተግባር:-

- ፆታን በአማከለ ሁኔታ ቅድሚያ ለሚሰጣቸው የግብርና ዘርፍ፣ የሰብል ኤይነትና ቴክኖሎጂ ዙርያ መረጃ መሰብሰብና መተንተን፡፡ ይህም ማለት የስራ ጫናን፣ ገበያን፣ ውሰኔ ሰጪነትንና ተጠቃሚነትን በተመለከተ ያሉ አጠቃላይ የፆታ መረጃዎችን ይሆናል

- የአገልሎት ተጠቃሚነትንና ለመረጃ ምንጮች ቅርበትን በተመለከተ የፆታ ልዩነት የሚያመጣውን ተጽዕኖ ማጤን (ለምሳሌ:- የኤክስቴንሽን ተጠቃሚ ከመሆን አንፃር)

- የፆታ ልዩነት በማሕበራዊ ግንኙነትቶች፣ በቡድን አባልነት እና በውሳኔ ሰጪነት ዙሪያ የሚያስከተለውን ችግር ማጥናት

2. ዓላማ:- ስለ ስርዓተ ፆታ ያለውን ግንዛቤ ማሳደግ

ተግባር:-

- በማንኛውም ደረጃ ላይ የሚገኙ፣ የአመራር አካሎች ያላቸውን የስርዓተ ፆታ ግንዛቤ ለማሳደግ (በስብሰባ፣ በአውደጥናቶች ወዘተ) ይቻል ዘንድ አግባብ ካላቸው አጋር ድርጅቶችም ሆነ ተቋማት ጋር በትብብር መስራት

- በወረዳ ደረጃ ላሉ ማናቸውም ክፍሎች የሚሰጡ የአሰልጣኞች ስልጠናዎች በዝቅተኛ የመስተዳደር እርከን ላሉ የኀብረተሰብ ክፍሎች የሚሰጡት የስርዓተ ፆታ ግንዛቤ ስልጠናዎችና ትምህርቶች አስተማማኝ መሆን ይኖርባቸዋል

- በወረዳ የንባብ ቤቶችና የግብርና ማሰልጠኛ ማዕከላት ውስጥ በአካባቢው ቋንቋ የተተረጎመ በቂ የፅሁፍ መረጃ እንዲኖር መርዳት

- በእያንዳንዱ የአይ ፒ ኤም ኤስ አውደ ጥትና የመስክ እንቅስቃሴ ውስጥ ስለ ስርዓተ-ፆታ የሚያስተምሩ ርዕሶች ሊካተቱ የሚችሉበትን መንገድ መፍጠር

3. ዓላማ:- በአይ ፒ ኤም ኤስ የተግባር እንቅስቃሴዎች አማካኝነት ስርዓተ ፆታን ማጐልበት

ሴቶች ለንብረት ያላቸውን ቅርበትና ቁጥጥር ማሳደግ

ተግባር:-

- ሴቶች በሚያደርጉት የግብርና ስራ እንቅስቃሴ ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉበትን መንገድ ከአጋር ድርጅቶች ጋር በመሆን ማመቻቸት (ለምሳሌ የኤክስቴንሽን ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉበትን መንገድ መምከር፣ ብድርና ግብዓቶችን ሊጠቀሙ እንዲችሉ ማገዝ)

- ሴቶችና በእማውራዎች የሚተዳደሩ ቤተሰቦችን የአዳዲስ ቴክኖሎጂ ውጤቶች ተጠቃሚ እንዲሆኑ አልሞ መስራት

- በመረዳዳት መንፈስ ላይ የተመሰረቱ የሴት ማህበራትን በማደራጀት የብድርና ቁጠባ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማስቻል

## ሴቶች ለእውቀትና ለሙያዊ ክህሎት ያላቸውን ቅርበት ማሳደግ

ተግባር:-

- ሴቶችን በስልጠናዎች ማሳተፍ (ማካተት)
- የሴቶችን ተሳትፎ ለማሳደግ የተለያዩ የስልጠና ስልቶችን መጠቀም (ለምሳሌ- ከባሎቻቸው ጋር ስልጠና የሚካፈሉበትን እድል መፍጠር፣ ለሴቶች ብቻ የታሰቡ ስልጠናዎችን ማዘጋጀት፣ የስልጠና ቦታዎችና ሰዓት ለሴቶቹ ምቹ እንዲሆኑ ማድረግ)
- ለጉልማሶችና ለሴቶች የመሠረተ ትምህርት በማመቻቸት ድጋፍ መስጠት
- ወንዶችና ሴቶች የገንዘብ አጠቃቀምና ቁጠባ ዘዴን እንዲያውቁ ማስተማር
- በመረዳዳት መንፈስ ላይ የተመሠረቱ የሴት ማህበራትን የልምድ መለዋወጫ መድረክ እንዲሆኑ መርዳት

## ሴቶች ገበያ ቀመስ የእርሻ ምርቶችን በማምረት ረገድ ያላቸውን ተሳትፎ ማጉልበት

ተግባር:-

- በገበያ ተፈላጊ የሆኑ ምርቶችን የሚ ያመርቱ ሴቶች ተሰባስበው ምርቶቻ ቸውን በመጠን የሚያሳድጉበትንና ገበያን ሰብረው የሚገቡበትን አቅም መፍጠር ማስቻል
- በመረዳዳት መንፈስ ላይ የተመሠረቱ የሴቶች ማህበራትን ወደ አምራችና ገበያ ፈጣሪነት አቋም በማሸጋገር በራሳቸው የገበያ መረጃ መለዋወጥ የሚችሉበትን ሁኔታ መፍጠር

## ሴቶች በቤተሰብ ውስጥ በአርሶ አደሮች መሃል እንዲሁም በአካባቢያቸው በሚገኙ ማህበራት ውስጥ ያላቸው የውሳኔ ሰጪነት ሚና እንዲያጠናክሩ መርዳት

ተግባር:-

- ሴቶችን በቡድን በማደራጀት ስለ መልካም የአስተዳደር ብቃት፣ በራስ የመተማመን መንፈስን ስለ ማጉልበት እንዲሁም የመልካም ተደራዳሪነትን ጥበብ ማስተማር
- ሴቶች በመረጃ ላይ የተመሠረተ ውሳኔ ሊሰጡ የሚችሉበትን ብቃት እንዲያገኙ የሚረዳ እቅድ መንደፍ

## የስራ ጫናንና ጉልበትን ሊቀንሱ የሚችሉ አዳዲስ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን በማስተዋለቅ የሴቶቹን አኗኗር ማሻሻል

ተግባር:-

- የሴቶችን ምርታማነት የሚያጉለብቱና
- የቤት ውስጥ የስራ ጫናን ሊያቃልሉ የሚችሉ አዳዲስ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ለይቶ ማቅረብ
- ሴቶች የቴክኖሎጂ ውጤቶችን በማስተዋወቅና በመጠቀም እንዲሳተፉ በማድረግ የቴክኖሎጂን ጠቀሜታና በህይወታቸው ላይ እያመጣ ያለውን ለውጥ እንዲያጤኑ ማስቻል
- በፆታ መሀከል ያለውን የሥራ ጫና ሚዛናዊ ለማድረግ ህብረተሰቡ የያዘውን የተሳሳተ አመለካከት እንዲቀየር ማድረግ
- የተቀራረጡ የግብርና ተግባራትን የተን ተራሰ የስራ ጉልበት ፍላጐት ስሌት ወ ደተሳሰተ የስራ ኃይል ፍላጐት



ትንበያ ስለሚያመራ ይህንኑ ለማረም እንዲቻል አጠቃላይ የግብርና ስራው የሚፈልገውን ጉልበት አስቀድሞ መገመትና እንደአስፈለጊነቱ የሚፈልገውን ጉልበት አስቀድሞ መገመትና እንድአስፈለጊነቱ ተጨማሪ ጉልበት በቅጥር ወይም በሌላ ዘዴ ሊገኝ የሚችልበትን መንገድ ማፈላለግ

4. ዓላማ:- ስርዓተ ፆታን ለማስረጽ የሚወስዱ ተግባራዊ እርምጃዎች

ሴቶች በተለያዩ ተግባራት ውስጥ ካላቸው ተሳትፎና ካላቸው የውሳኔ ሰጪነት ቦታ አንፃር የስብጥር ጣሪያ ማበጀት

ተግባር:-

- የሴቶችን ተሳትፎ የሚያሳይ የስብጥር ጣሪያ ምሳሌ:- 50% የሰብል ገበያ ጥናት ሰልጣኝ ሴቶች ይሆናሉ 30% የመስክ ተሳታፊዎች ሴቶች ይሆናሉ

- የሴቶችን የውክልና የስብጥር ጣሪያ የሚያሳይ፡ 40% ያህሉ ቢያንስ ሴቶችን የወከሉ ይሆናሉ

ከሴቶች ጋር ለመስራት ፈቃደኛ የሆኑ ልምድ ያካበቱ መያድ (መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን) መምረጥ

ተግባር:-

- አብረው ሊሠሩ ይችላሉ ብለን ያሰብናቸውን ድርጅቶች የስራ እንቅስቃሴ፣ ልምድና አቅም በሚገባ በመመርመር ስለ ፆታ እኩልነት ያላቸውን አቋምና ቁርጠኝነት መወሰን

- የሥራ አጋሮቻችን በየስራ ኘሮግራሞቻቸው ውስጥ የስርዓተ ፆታን በሕብረተሰቡ ውስጥ ለማስረጽ የሚረዱ ተግባራትን እንዲያካትቱ ማበረታታት

ለተግባራዊነት የሚረዱ አዲስ አጋርነትና ግንኙነት መፍጠር

ተግባር:-

- አዳዲስ አጋሮቻችን በአይ ፒ ኤም ኤስ ተግባራት ውስጥ እንዲሳተፉ ማድረግ (ለምሳሌ:- የሴቶች ጉዳይ ቢሮ በአውደ ጥናቶችና በስልጠናዎች ይሳተፋል)

- የጋራ እቅዶች ከአዳዲስ አጋሮች ጋር የሚነደፉበትን መንገድ ማመቻቸት

- አዲሶቹ አጋሮች ንብረቶቻቸውንና ያላቸውን ሀብት በጋራ በመጠቀም እንዲሰሩ ማበረታታት

የስራ አፈፃፀምና የለውጥ መለኪያዎችን (አመላካቾችን) ፆታን በአናጠለ መልኩ ማሰባሰብ

ተግባር:-

- የመረጃ ዘገባዎች አሰባሰባቸውና የትንታኔ ሂደታቸው ፆታን አናጥሎ መሆን ይኖርበታል